## እይታዬ

በዚህ ዓምድ ማንኛውም ግለሰብ በፈለገው ጉዳይ ላይ በሚመቸው መንገድ አስተያየቱን መጻፍ ይችላል በዚህ ዓምድ ላይ የሚወጡ ጽሑፎች የዝግጅት ክፍሉ ኀሳብ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም::

# ዳንኤልና ነጻነት

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም
መጋቢት 2000



በጥቅምት 1998 ዓ.ም ላይ የሚያዝያ 1997 ዓ.ም የሕዝብ ስብሰባ እና ተከታትሎ የመጣው ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነጻነት ያለውን ቁርጠኛ ፍላጎት አሳየ፤ ተደላድለው የነበሩ ወንበሮችን አነቃነቀ፤ በትምክህት አብጠው የነበሩትን ሁሉ ልባቸውን በፍርሃት አርበደበደው፤ ከታች መሰረት፣ ከጎን ምሰሶ፣ ከላይ ጣሪያ የሌላቸው መሆናቸውን ያለጥርጥር እንዲገነዘቡ አደረጋቸው፤ ጭካኔ ከፍርሃት ተለወደ:: የፍርሃት ልጅ ያስከተለው መዘዝ ወዳጅንና ጠላትን የመለየት ችሎታንም እስከመንሳት ደረሰ::

በዚህን ጊዜ ነው አንዳንድ የቅንጅት መሪዎች፣ አንዳንድ የቅንጅት አባሎች፤ አንዳንድ የቅንጅት ደጋፊዎች፣ አንዳንድ ጋዜጠኞች፣ አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መሪዎችና አንዳንድ በውጭ አገር የሚኖሩ ዜጎች ቅጡ በጠፋ መልክ የተካኑት ፣ተይዘው የታሰሩትና በከፉ ወንጀል የተከሰሱት:: አንድ አድማ ተብሎ ከተከሰሱትና ከማይተዋወቁት ሰዎች ውስጥ አብዛኞቹ በተለያየ መንገድ ከእስር ቤት ወጥተዋል፤ ዛሬ በወህኒው ቤት የቀሩት ዳንኤልና ነፃነት ናቸው::

ዳንኤልና ነጻነትን ያወቅኳቸው ቃሊቲ ነው፤ ሁለቱም የሕግ ባለሙያዎች ሲሆኑ በትምህርታቸውም የገፉ ናቸው፤ ጠባያቸውም መልካም አስተዳደግን የሚያንፀባርቅ ጨዋነት የተሞላበት ነው:: ከአንደበታቸው ክፉ ነገር አይወጣም፤ አካላቸውም ጸረ-ድብድብ ነው:: የአዕምሮና የመንፈስ ወኔአቸው ግን ከአካላቸው በጣም ይገዝፋል፤ ብስለታቸወም ከእድሜአቸው በጣም ይልቃል::

እነዚህ ሁለት ሰዎች የቅንጅት ፓርቲ አባሎች አይደሉም፤ ስለዚህም የቅንጅት አባሎች የቀረበባቸውን የተደረተ ክስ አንቀበልም፤ አንከላከልም፤ ሲሉ ዳንኤልና ነፃነት ለመከላከል ቆረጡ:: የዋስ መብታቸውን ጠይቀው በተደጋጋሚ ተከለከሉ፤ አሁንም የቅንጅት ፓርቲ አባሎች ባለመሆናቸው በሽምግልናውም ሆነ በምህረቱ አካሄድ ውስጥ አልነበሩም፤ ስለዚህም ሙግታቸውን በሰለጠኑበት ሕግ ቀጠሉ:: ከሁለት ዓመት ያህል እስር በኋላ ሁለት ዓመት ተኩል ተፈረደባቸው:: በሕጉ መሰረት በአመክሮ ከእያንዳንዱ ዓመት ሦስት ወሮች ይቀነሱለታል፤ በዚህ ሂሳብ ነፃነትና ዳንኤል ከተፈረደባቸው የሁለት ዓመት ተኩል ቅጣት ላይ የአሥር ወሮች ቅናሽ ተነስቶላቸው ይወጡ ነበር፤ አሁንም በእስር ላይ ስለሆኑ ከታሰሩ ወደ 29 ወሮች የተጠጉ ይመስለኛል:: ከዚያም አልፎ በጣም አስቸጋሪ ነው ወደሚባልበትና በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ እስረኞች ወደሚገኙበት ግቢ ተዛውረዋል ይባላል:: እንደሚሰማው ከሆነ ለዚህ ሁሉ ዋናው ምክንያት የዳንኤልና የነጻነት አጉል ጠባይ ነው:: እንኳን ወጣቶች ሽማግሌዎቹም የሚያከብሯቸው፤ የዱሮ ሰዎች እንደሚሉትም «ስኳር አፋቸው ውስጥ የማይሟሟ ሰዎች ምን አጉል ጠባይ ተገኘባቸው?» አዘውትረው ሕጋዊ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ፤ መልስ የሌላቸው ሕጋዊ ጥያቄዎችን ማቅረብ ፈተና መስጠት ይመስላል:: በእስር ቤቱ መመዘኛ ፈተናውን የሚወድቀውና አጉል ጠባይ አለው የሚባለው ጥያቄውን ሊመልስ ያልቻለው ሳይሆን ጥያቄውን የሚያቀርበው ነው:: ምናልባት ሌላው አጉል ጠባያቸው ልበ ሙሉነታቸው ሊሆን ይችላል? ከሁሉም በላይ የሚገርመውና ሕጉንም እስር ቤቱንም ትዝብት ላይ የሚጥለው በአንድ ክስ ሁለት ዓይነት ፍርድ ከተሰጠ በኋላ እድሜ ልክ የተፈረደባቸው ከእስር ቤቱ ወጥተው ሁለት ዓመት ተኩል የተፈረደባቸው እስከዛሬ እስር ቤት መቆየታቸው ነው::



ለነገሩ ፍርድ ቤት ነፃ ያላቸው ሰዎችም በወህኒ ቤቱ ይከርማሉ:: እስረኞች ከፍርድ ቤት ሲመለሱ ነጻ የተባለውን እያቀፉ መሳምና ደስታን በተለያየ መልክ መግለፅ የተለመደ ነው፤ ይህ ከሆነ በኋላ በሳምንቱም፣ በወሩም እዚያው ሲታይ አይ አጉል ጠባይ! ያሰኛል::

የግል ስሜትን አስወግዶ በአገር ደረጃ ማሰብ ቢቻል ፍርድ ቤት ከወሰነውና ሕጉ ከሚያስገድደው ውጭ አንድ ቀንም በእስር ቤት መቆየት የለበትም:: እስረኛውን ከፍርድ ውጭ ማቆየት በየቀኑ የገንዘብ ወጪን ያስከትላል፤ እስር ቤቱ ይህን በጭራሽ አይመለከተውም፤ እልህን ለመወጣትና ሥልጣንን ለማሳየት እስረኞችን በጊዜው ከመፍታት ማዘግየት ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም:: ለብዙ ዓመታት ሊያርማቸው ያልቻላቸውን እስረኞች ለጥቂት ወራት መቅጣት ሰውን መጉዳት ፋይዳ ያለው ነገር አድርጎ እንደመውሰድ ይቆጠራል::

እስር ቤቱ ማረሚያ ቤት ቢሆን ኖሮ ዳንኤልንና ነፃነትን በአርአያነት ብቻ ሳይሆን በአስተማሪነት ሊጠቀምባቸው ይችል ነበር:: ዳንኤልና ነፃነት በግፍ፣ ስለግፍ ተምረው የተሻሉ ሰዎች ሆነው ይወጣሉ፤ መማር የሚችሉ ናቸውና:: እስር ቤቱ ግን ትምህርትን እንደ አጉል ጠባይ እየቆጠረ ይቀጥላል፤ የእውነት ጸሐይ እስኪወጣለት::